የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ መጋቢት ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 28
ADDIS ABABA, 13th .March ,2017

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፮/፪ሺ፱ ዓ.ም
ለጅማ-ጭዳ እና ለሶዶ-ሳውላ የመንገድ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …………………ገጽ ፱ሺ፭፻፸፱

**CONTENT**

Proclamation No. 996/2017
**African Development Fund Loan Agreement for Financing Jimma-Chida and Sodo-Sawla Road upgrading project Ratification Proclamation** ……………………..page 9579

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፮/፪ሺ፱

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለጅማ-ጭዳ እና ለሶዶ-ሳውላ የመንገድ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ፳፭ ሚሊዮን ፭፻፹፱ ሺ ፰፻፷፫ ዩ.ኤ (ሃያ አምስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ስድሳ ሦስት ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል ጥር ፳፪ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፴ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

## PROCLAMATION No. 996/2017

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

**WHEREAS, a loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund Provided to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of U.A. 25,589,863 (Twenty five million five hundred eighty nine thousand eight hundred sixty three units of Account) for financing Jimma -Chida and Sodo-Sawla Road upgrading project was signed in Addis Ababa on 30th day of January 2017;**

**WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on the 7th day of February 2017;**

**NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:**

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ማ-ጭዳ እና ለሶዶ-ሳውላ የመንገድ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፮/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል ጥር ፳፪ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 2100150036498 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ዩ.ኤ ፳፭ ሚሊዮን ፭፻፹፱ ሺ ፰፻፷፫ (ሃያ አምስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ስድሳ ሦስት) ዩኒትስ ኦፍ አካውንት በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

**This Proclamation m**

**Development Fund Loan Agreement for financing Jimma-Chida and Sodo-Sawla Road upgrading project Ratification Proclamation No. 996/2017".**

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

**The Loan Agreement Number 2100150036498 signed in Addis Ababa on the 30th day of January 2017 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund is hereby ratified.**

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

**The Ministry of Finance and Economic Cooperative is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of U. A. 25,589,863(Twenty five million five hundred eighty nine thousand eight hundred sixty three units of amount) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.**

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 13th day of March , 2017.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**